# የመገልገያ ፍጆታ ክፍያዎችን ለመክፈል እገዛ ይፈልጋሉ?

**የሲያትል ከተማ ብርሃን (ኤሌክትሪክ) ወይም የሲያትል የህዝብ መገልገያ (ውሃ/ፍሳሽ/ቆሻሻ) ሂሳብዎን ለመክፈል ከኋላ ነዎት ወይስ እየታገሉ ነው?**
እኛ እርስዎን ለመርዳት እዚህ አለንልዎት! ደንበኞቻችን እንዲታገዙ እና የፍጆታ ሂሳቦቻቸውን መክፈል እንዲችሉ ለማገዝ የእዳ አከፋፈል አማራጮችን እና የክፍያ እርዳታ ፕሮግራሞችን እናቀርባለን።

## የክፍያ ዕቅዶች

**የሲያትል ከተማ ብርሃን እና የሲያትል የህዝብ መገልገያ ክፍያ ዕቅዶች**
በሲያትል ከተማ መብራት (ኤሌክትሪክ) እና በሲያትል የህዝብ መገልገያዎች (ውሃ፣ ፍሳሽ እና ቆሻሻ) የመገልገያ ፍጆታ ሂሳቦችዎ አልፎብዎት ከሆነ፣ ለሁሉም የነዋሪዎች እና የንግድ ደንበኞች ጊዜ የክፍያ እቅዶችን ያቀርባሉ።
በክፍያ እቅድ፣ በጊዜ ሂደት ቀሪ ሂሳብዎን ትንሽ በትንሽ ክፍል መክፈል ይችላሉ። አዲሶቹን የመገልገያ ፍጆታ ሂሳቦችን እና የክፍያ እቅድ ክፍያዎችን በሰዓቱ በመክፈል፣ ባለመክፈል አገልግሎቶችን ማቋረጥ እንደገና ስንጀምር የርስዎ የመገልገያ ፍጆታ አገልግሎቶችን ያቆያሉ።

## የክፍያ ሂሳብ እርዳታ ፕሮግራሞች

የመኖሪያ ቤት ደንበኛ ከሆኑ እና የገቢ ብቁነት መስፈርቶችን ካሟሉ ለቀጣይ እና ለአደጋ ጊዜ የክፍያ መጠየቂያ እርዳታ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

### የመገልገያ ፍጆታ ቅናሽ ፕሮግራም

ለወደፊቱ የሲያትል ከተማ ብርሃን ሂሳቦችን 60% ቅናሽ እና ለወደፊቱ የሲያትል የህዝብ መገልገያ ክፍያዎችን 50% ቅናሽ የሚያሰጥ፣ በገቢ ብቁ የሆኑ ደንበኞች በሲያትል ከተማ የመገልገያ ፍጆታ ቅናሽ ፕሮግራም መመዝገብ ይችላሉ።

### የአደጋ ጊዜ የክፍያ ሂሳብ እርዳታ ፕሮግራሞች

**የሲያትል ከተማ መብራት**
በመብራት የክፍያ ሂሳቡ ወደ ኋላ ቀርተው ከሆነ እና የእርስዎ አገልግሎት የመዘጋት ስጋት የሚደርስበት ክሆነ የሲያትል ከተማ መብራት የድንገተኛ ጊዜ የክፍያ ሂሳብ እርዳታ ፕሮግራም ሊረዳ ይችላል። ለገቢ ብቁ የሆኑ ደንበኞች ያለፈውን ቀሪ ሂሳባቸውን ለመቀነስ በድንገተኛ እርዳታ በአንድ ቀን መቁጠሪያ አመት እስከ $710 ዶላር ሊያገኙ ይችላሉ። ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች በአንድ ቀን መቁጠሪያ አመት እስከ $1,420 ዕርዳታ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

**የሲያትል የሕዝብ መገልገያዎች (SPU)**
የውሃ፣ የፍሳሽ ማስወገጃ ወይም የቆሻሻ የክፍያ ሂሳብ ወደ ኋላ ቀርተው ከሆኑ እና የእርስዎ አገልግሎት የመዘጋት ስጋት የሚደርስበት ክሆነ የሲያትል የህዝብ መገልገያዎች የድንገተኛ ጊዜ እርዳታ ፕሮግራም ሊረዳ ይችላል። በገቢ ብቁ የሆኑ ደንበኞች ያለፈውን ቀሪ ሂሳባቸውን ለመቀነስ በዓመት እስከ $537 የድንገተኛ ጊዜ እርዳታ ሊያገኙ ይችላሉ። ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች በአንድ የቀን መቁጠሪያ አመት እስከ $1,074 ሊያገኙ ብቃት ሊኖራቸው ይችላሉ።

## አግኙን

በመገልገያ ፍጆታ የክፍያ ሂሳቦች ወደ ኋላ ከቀሩ ወይም በየወሩ ክፍያዎችን ለመፈጸም እየታገሉ ከሆነ፣ የመገልገያ አገልግሎቶችዎን ለማቆየት፣ የክፍያ እቅድ ለማዘጋጀት እና ለክፍያ መጠየቂያ እርዳታ ለማመልከት ከእርስዎ ጋር ልንሰራ እንችላለን።

**በመስመር ላይ ይጎብኙን።**
የክፍያ እቅድ ለማዘጋጀት፣ ለክፍያ መጠየቂያ እርዳታ ለመመዝገብ እና ቀሪ ሂሳብዎን ለመክፈል
በ seattle.gov/UtilityBillHelp ላይ ይጎብኙን።

**ለደንበኛ አገልግሎት ቡድናችን ይደውሉ**
ክፍያ ለመፈጸም፣ የክፍያ እቅድ ስለማዘጋጀት ተወካይ ለማነጋገር፣ ወይም ለክፍያ መጠየቂያ ፕሮግራሞች ለማመልከት (ከሰኞ እስከ አርብ፤ ከጠዋቱ 7:30 - 6:00 ምሽት) በ (206) 684-3000 ይደውሉልን። ከእንግሊዝኛ ውጭ በሌላ ቋንቋ እርዳታ ከፈለጉ የደንበኛ እንክብካቤ ቡድናችን በመረጡት ቋንቋ ያለምንም ወጪ ይረዳዎታል።

**የደንበኛ አገልግሎት ማዕከሎቻችንን ይጎብኙ**
የክፍያ ሂሳቦችዎን በአካል፣ በጥሬ ገንዘብ፣ በቼክ ወይም በክሬዲት ካርድ ለመክፈል የደንበኛ አገልግሎት ማዕከልን ይጎብኙ።

**የሲያትል ከተማ መብራት የሰሜን አገልግሎት ማዕከል**
1300 N 97th Street, Seattle, WA 98103 | ሰኞ – አርብ፤ ከጧት 8:30 – 4:30 ከሰዓት | (206) 615-06004

**የሲያትል ከተማ መብራት የደቡብ አገልግሎት ማዕከል**
3613 4th Avenue S, Seattle, WA 98134 | ሰኞ – አርብ፤ ከጧት 8:30 – 4:30 ከሰዓት | (206) 386-4200

**ባላርድ የአገልግሎት ማዕከል**
5604 22nd Ave NW, Seattle, WA 98107 | ማክሰኞ – አርብ፤ ከጧት 9:00 – 5:00 ከሰዓት | (206) 684-4060

**የማዕከላዊ ወረዳ አገልግሎት ማዕከል**
464 12th Avenue, First Fl, Seattle, WA 98122 | ማክሰኞ – አርብ፤ ከጧት 9:00 – 5:00 ከሰዓት | (206) 684-4767

**የመሃል ከተማ የአገልግሎት ማዕከል**
700 Fifth Avenue, Seattle, WA 98104 | ሰኞ – አርብ፤ ከጧት 8:30 – 4:00 ከሰዓት | (206) 684-3000

**የሌክ ሲቲ አገልግሎት ማዕከል**
12525 28th Ave NE, 2nd Fl, Seattle, WA 98125 | ማክሰኞ – ቅዳሜ፤ ከጧት 9:00 – 5:00 ከሰዓት | (206) 684-7526

**የደቡብ ምስራቅ አገልግሎት ማዕከል**
3815 S Othello St, Suite 105, Seattle, WA 98118 | ሰኞ – ቅዳሜ፤ ከጧት 9:00 – 5:00 ከሰዓት | (206) 386-1931

**የደቡብ ምዕራብ አገልግሎት ማዕከል**
2801 SW Thistle St, Seattle, WA 98126 | ሰኞ – አርብ፤ ከጧት 9:00 – 5:00 ከሰዓት | (206) 684-7417

**የዩኒቨርሲቲ አገልግሎት ማዕከል**
4534 University Way NE, Seattle, WA 98105 | ማክሰኞ – ቅዳሜ፤ ከጧት 9:00 – 5:00 ከሰዓት | (206) 684-7542)



Seattle

**በ seattle.gov/UtilityBillHelp ላይ የበለጠ ይወቁ።**